ማድረግ የሚገባቸውን የመላው ሰውነት ምርመራ ሲያደርጉ የአፈ-ማሕፀንም ምርመራ አያዘወትሩ ይሆናል። ኪንታሮቱም በአፈ-ማሕፀን ላይ ሊበቅል ስለሚችል፣ አዘውትሮ መመርመሩ በጣም አስፈላጊ ነው።

## ሕክምና፡-

ኤችፒቪ ምንም መድሐኒት የለውም። ኪንታሮቶቹ በሓኪም ተቆርጠው ሊነሱ ይችላሉ፣ አንዳንዴም እንዲሁ በራሳቸው የሚጠፉበት ጊዜ አለ፣ ተደብቀውም የሚኖሩበትና ለሕይወት አደገኛ የሚሆኑበትም ሁኔታ ሊኖር ይችላል። ለዚህም ነው አዘውትሮ የጤና ምርመራ ማድረግ የሚገባ።

## መከላከያው፡-

እንደሌሎቹ የግብረ-ስጋ በሽታዎች ከግብረ-ስጋ ፈጽሞ በመራቅ፣ ወይም በሽታው ከሌለበት አንድ ሰው ብቻ ተቆጥቦ ግብረ-ስጋን በመፈጸም ለመከላከል ይቻላል። ይህ በሽታ ኮንዶምን በመጠቀም ለመከላከል አይቻልም።

## ውርዴ ወይም ፈንጣጣ፡-

ውርዴ በግብረ-ስጋ የሚተላለፍ የባክተሪያ በሽታ ነው። ውርዴ ከሰው ወደ ሰው የሚተላለፈው የውርዴውን ቁስል በቀጥታ ከነኩት ነው።

## ምልክቶች፡-

ውርዴ ብዙ ምልክቶች ሲኖሩት፣ የሌላ በሽታ ምልክቶች ሊመስሉና ሊያታልሉም ይችላሉ። ውርዴ ሦስት ደረጃ አሉት።

## 1ኛ ደረጃ፡-

በተጋባ ከ 10 እስከ 90 ቀናት ባሉት ውስጥ የበሽታው የመጀመሪያ ምልክቶች ይታያሉ። የውርዴ ቁስል ይወጣል፣ ካልታከመም የውርዴው ቁስል እየባሰ ይሄዳል።

## 2ኛ ደረጃ፡-

በማንኛውም ቦታ ከቆዳ ላይ ቀይና ፍም የመሰለ ነገር ይወጣል። ግን ምንም የማሳከክ ስሜት የለበትም። ካልታከመ በሽታው እየባሰ ይሄዳል።

3ኛና የመጨረሻው ደረጃ፡- ከውጭ ያሉት ምልክቶች ሁሉም ይጠፋሉ። የበሽተኛው ገላ ስሜት መጥፋት ይጀምራል፣ ከአእምሮ ድክመትም ይደርሳል፣ የአካላት ማንቀሳቀስም ሊያቅት ይጀምራል። ሕክምና ካላገኘ ውርዴ ሞትን ያስከትላል።

## ሕክምና፡-

በመጀመሪያ ደረጃ የሚገኝ ውርዴ በቀላሉ ሊታከምና ሊድን ይችላል። ግን በሓኪም ትእዛዝ እንጂ ከፋርማሲ ማንም ሰው የሚገዛቸው መድሓኒቶች ባክተሪያውን ሊያጠፉት አይችሉም። ሓኪም የሚያዝዘው መድሓኒት ውርዴውን ቢያጠፋውም እንኳን በአካል ላይ ለደረሰው ጉዳትና ጠባሳ ለማከም አይቻል ይሆናል።

## መከላከያው፡-

ውርዴን መከላከል ይቻላል። እንደ ሌሎች የግብረ-ስጋ (ኤስቲዲ) በሽታዎች ውርዴም ከግብረ-ስጋ ፈጽሞ በመገለል፣ ወይም ሕመሙ ከሌለበት ሰው ብቻ ግብረ-ስጋን በመፈጸም ለመከላከል ይቻላል። ኮንዶምን በመጠቀም ግን ሕመሙን ለመከላከል አይቻልም።

• • •

**ተጨማሪ ማስረጃ በኢንተርኔት ለማግኘት የሚከተሉትን ይመልከቱ፡-**

Body Health Resources Corporation
www.thebody.com
American Social Health Organization
www.iwannaknow.org and
www.ashastd.org

The Centers for Disease Control National Prevention Information Network
www.cdcnpin.org

**በስልክም መረጃ ሲያስፈልግ፡-**

CDC National STD Hotline
1-800-227-8922
24 hours a day, 7 days a week
CDC National AIDS Hotline
1-800-342-AIDS (1-800-342-2437)
24 hours a day, 7 days a week
National Women's Health Information Center, a part of the U.S. Department of Health and Human Services
1-800-994-9662

• • •

Information for this brochure was adapted from materials developed by:
The Centers for Disease Control and Prevention (CDC)
Body Health Resources Corporation
American Social Health Association

ይህ በስደተኞች መቋቋሚያ የጤና ክፍልና በሰብአዊ አገልግሎት ቢሮ ከተገኘው ገንዘብ የተዘጋጀ ጽሑፍ ነው።

**CONTACT INFORMATION:**
**riht@uscridc.org**
**U.S. Committee for Refugees and Immigrants**
**1717 Massachusetts Ave., NW**
**Suite 200**
**Washington, DC 20036**
**Phone: 202 • 347 • 3507**
**Fax: 202 • 347 • 7177**
**www.refugees.org**



# በግብረ-ስጋ ስለሚተላለፉ በሽታዎች ሁሉም ሰው ማወቅ የሚገባው፡-

(STD-Amharic)

U.S. COMMITTEE FOR REFUGEES AND IMMIGRANTS
USCRI
**www.refugees.org**
*Protecting Refugees, Serving Immigrants, Upholding Freedom since 1911*

HEALTHY LIVING

* * * Translated by G. E. Gorfu & Asc.

# የግብረ-ስጋ በሽታን (ኤስቲዲ) መከላከል ይቻላል!

## ቅላሚድያ

ቅላሚድያ ሊድን የሚችል፣ በግብረ-ስጋ የሚተላልፍ በሽታ ነው። ቅላሚድያ ከሰው ወደ ሰው በብልት፣ በቂጥ፣ ወይም በአፍ በመነካካት ይጋባል። በወሊድም ጊዜ ከእናት ወደ ሕፃን ሊጋባ ይችላል። በሃያና በሠላሳ ዓመት ዕድሜ መካከል የሆኑትና ግብረ-ስጋን የሚያዘወትሩ ሁሉ የቅላሚድያ ምርመራ ማድረግ ይገባቸዋል። ያልታከመ የቅላሚድያ በሽታ በወንድም ሆነ በሴት የወሊድ ብልቶች ብዙ ጠንቅን አምጥቶ እስከ መኻንነት፣ ለማርገዝም አለመቻል ድረስ ያደርሳል።

### ሕመሙና ምልክቶቹ:-

በሴቶች:- ብዙ ሴቶች ምንም ምልክት አያሳዩም። ቢታይም በጣም ትንሽ ነው።

በወንዶች:- ብዙ ወንዶች ምንም ምልክት አያሳዩም። ቢታይም በጣም ትንሽ ነው። አንዳንድ ወንዶች በብልታቸው ፈሳሽ ነገር ሊታይ ይችላል።

### ሕክምና:-

ቅላሚድያ በአንቲባዮቲክ ሊታከምና ሊድን ይችላል። ከታመመው ሰው ጋር የተገናኙ ሁሉ በሓኪም መታከም ይኖርባቸዋል።

### መከላከያው:-

- ፈጽሞ ከግብረ-ስጋ መራቅ
- ሕመሙ ካለበት ሰው ጋር በግብረ-ስጋ አለመገናኘት
- በትክክልና ሳያቋርጡ የላስቲክ ኮንዶምን (ለወንድም ሆነ ሴት) መጠቀም

## ጎኖርያ (ጨብጥ)

ጎኖርያ ታክሞ የሚድን የግብረ-ስጋ (ኤስቲዲ) በሽታ ነው። የሚተላለፈውም በብልት፣ በቂጥና፣ በአፍ ነው። ጎኖርያ በወሊድም ጊዜ ከእናት ወደ ሕፃን ሊተላልፍ ይችላል።

ጎኖርያ ከብዙ ሕመምና የጤና ችግሮች ላይ ሊያደርስ ይችላል። ካልታከሙት ጎኖርያ ልክ እንደ ቅላሚድያ እስከ መኻንነት ጭምር ይዳርጋል።

### ምልክቶች:-

በሴቶች:- ብዙ ሴቶች ምንም ምልክት አያሳዩም። ምልክቶችም ቢኖሩ በጣም ቀላል ናቸው። እነዚህም:-

- ሽንት በሚሸኑ ጊዜ የማቃጠል ስሜት
- ያለተለመደ ፈሳሽ ከብልት ሊወጣ ይችላል

በወንዶች:- ብዙ ወንዶች ምንም ምልክት አያሳዩም። ከታዩም በሦስት እስከ አምስት ቀናት ውስጥ ባሉት:-

- ሽንት ሲሸኑ የሚያቃጥል ስሜት
- በብልት ነጭ፣ ብጫ፣ ወይም አረንጓዴ መሳይ ፈሳሽ ነገር ሊታይ ይችላል።
- በአንዳንድ ወንዶች የቆለጦች ማበጥና ስቃይም ሊኖርባቸው ይችላል።

### ሕክምና:-

ጎኖርያ በአንቲባዮቲክስ ሊታከምና ሊድን ይችላል።

### መከላከያው:-

- ፈጽሞ ከግብረ-ስጋ መራቅ
- ሕመሙ ካለበት ሰው ጋር በግብረ-ስጋ አለመገናኘት
- በትክክልና ሳያቋርጡ የላስቲክ ኮንዶምን (ለወንድም ሆነ ለሴት) መጠቀም

## ሄርፒስ

ሄርፒስ፣ ሄርፒስ ሲምፕሌክስ ከተባለው ከአፍ (የአፍ ሄርፒስ) እና ከብልት (የብልት ሄርፒስ) የሚመጣ በሽታ ነው። ቆዳ ለቆዳ በመነካካት ከሰው ወደ ሰው ይተላለፋል። በሽታው በብዙ ሰው ላይ ይገኛል፣ ብዙዎችም በሽታው እንዳለባቸው ሳያውቁ፣ ወይም ሌላ ዓይነት በሽታ ሊመስላቸው ይችላሉ። ይህ በሽታ ምንም መድሓኒት የለውም።

### ምልክቶች:-

- በብዛት የሚታየው እንደ ብጉር የመሰሉ ጥቂት ችፍ ብለው ይወጡና ደርቀው በመቁሰል ይሰነጣጠቃሉ።
- በታመመው ሰው በሽታው ለሳምንት፣ ለወር፣ ለዓመታትም ምንም ምልክት ሳያሳይ ሊደበቅና ምልክቱም ፈጽሞ ላይታይበት ይችላል።
- በብዙ ሰው ምልክቶቹ አይታዩም፣ ወይም በጣም ቀላል ሆነው ሌላ ሕመም ሊመስሉ ይችላሉ።

### ሕክምና:-

ሄርፒስ ከያዘ መድሓኒት የለውም። በመድሓኒትም ለመከላከል አይቻልም።

### መከላከያው:-

- ፈጽሞ ከግብረ-ስጋ መራቅ። ግን ምንም ግብረ-ስጋን ያልፈጸሙም ሰዎች ሕመሙ ሊኖራቸውና ወደ ሌላም ሰው በመነካካት ብቻ ሊያጋቡት ይችላሉ።

## ጸሕተ/ኤይድስ

ጸሕተ (ጸረ-ሕዋስ ተዋጊ የተባለው ቫይረስ) ኤይድስን የሚያመጣ ነው። ጸሕተ ከደም፣ ከአባለ-ዘር፣ ከሴት ብልት ከሚወጡ ፈሳሾች፣ ወይም ከታመመች ሴት ከሚገኝ የጡት ወተት ይተላለፋል። ጸሕተን በቀላሉ ለመከላከል ይቻላል። የበሽታው ምልክት ፈጽሞ የማይታይባቸው ሰዎች ጸሕተ ሊኖርባቸውና ወደ ሌላም ሰው ሊያጋቡት ይችላሉ።.

### ምልክቶች:-

- በበሽታው የተለከፈ ሰው ሕመም ሳይኖርበት፣ ምንም የበሽታው ምልክትም ሳይታይበት ለብዙ ዓመታት ሊቆይ ይችላል።
- እንዲሁ በዓይን ብቻ አይቶ የጸሕተ በሽታ ያለበትን ሰው መለየት አይቻልም።
- የሓኪም ምርመራን ካላደረጉም ለማረጋገጥ አይቻልም።

ሕክምና:- የጸሕተ በሽታ ምንም መድሓኒት የለውም ለሕመሙ ግን ማስታገሻዎች አሉት። በተገቢ ሕክምናና ጤና ምግብን በመመገብ የጸሕተ በሽታ ያለው ሰው ረዥምና ጤና የሆነ ዕድሜ ሊኖር ይችላል። ጸሕተ ያላቸው ሴቶች ሲያረግዙ የቅድመ-ወሊድ እንክብካቤ በማድረግ በሽታው ወደ ሕፃኑ እንዳይጋባ ለመከላከል ይቻላል።

### መከላከያው:-

- ፈጽሞ ከግብረ-ስጋ መራቅ
- ሕመሙ ካለበት ሰው ጋር በግብረ-ስጋ አለመገናኘት
- በትክክልና ሳያቋርጡ የላስቲክ ኮንዶምን (ለወንድም ሆነ ለሴት) መጠቀም

## የሰብእ ፓፒሎማ-ቫይረስ (ኤችፒቪ) ወይም የብልት ኪንታሮት

የሰብእ ፓፒሎማ-ቫይረስ የተባለው በሽታ ከሰው ወደ ሰው በግብረ-ስጋ ይተላለፋል። ሕመሙ ለሞት እጅግ የሚያጋልጠውን የአፈ-ማሕፀንን ካንሰር ሊያመጣ ይችላል። የብልት ኪንታሮትም ያወጣል። ኪንታሮቱም በብልት ላይ፣ በአፈ-ማሕፀን፣ በቂጥ፣ በጭንም አካባቢ ሊወጣ ይችላል።

### ምልክቶች:-

- የሚበዙ የኤችፒቪ ሕመምተኞች ምንም ምልክት አይታይባቸውም።
- በአንዳንዱ ላይ የብልት ኪንታሮት ይወጣል። እነዚህም ለስላሳና ያበጡ፣ በብልት አካባቢ፣ በቂጥ፣ በቆለጥና፣ በጭንም ላይ ሊበቅሉ ይችላሉ።
- ሕመሙ በተጋባ በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ኪንታሮቱ ሊወጣ ይችላል።
  በሴቶች:- አንዳንድ ሴቶች በየዓመቱ

* * * Translated by G. E. Gorfu & Asc.